# በሰላማዊ ሰልፍ ሥም የተሰባሰቡ ቁማርተኞች

**ዮናስ** 08/14/13

Tower in the sky የዚያን ትውልድ ሁለንተናዊ ገፅታ ከተረኩ መፅሃፍቶች ሁሉ በይዘት ደረጃም ሆነ በኪናዊ እይታ ከሁሉም የላቀና ዘመኑን እስከ ግሣንግሱ በማሳየት የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ አሁንም መነጋገሪያነቱ እንደቀጠለ ስለመሆኑ ከገበያ የመጥፋቱ ብቻ ሳይሆን በርካታ ምሁራንም እየተነጋገሩበት መሆኑ ዓብይ ምስክር ነው፡፡

Tower in the sky ነገሬ ሳይሆን የዛሬው ጹሁፌ መነሻ ነው፡፡ የሸገር ካፌ አንደኛው ጠረጴዛም በዚሁ መነጋገሪያ በሆነውና ስነ ጹሁፋዊ ደረጃው ከፍ ባለው መጽሀፍ ላይ እንደተተረከው ያ ትውልድ በአብዮተኞች (Revolutionaries) በአድርባዮች (opportunist) እና በጆሊ (jolly jack) አቻ ቡድኖች ይገለፃል፡፡ jelly jack ወይም ከአራዳ ዘናጮች መሃል በወቅቱ የሚመደቡትና በአንድ ወቅት በአብዮተኞች ተማርከው አብዮቱን የተቀላቀሉትና ከዚያ እልቂት ተርፈው በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ በሸገር ካፌ አንደኛው ጠረጴዛ ላይ ከጋዜጠኛ ህይወት ፍሬስብሃት ጋር ታድመው የህይወት ተፈራን Tower in the sky በዶክተር ዳኛቸው ትርጓሜ “ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ” መፅሐፍ ላይ በርካታ ወጎችን አውግተውልናል፡፡ ታዲያ ለዛሬው ጹሁፌ መነሻ የሆነኝን ወግና ቁም ነገርም ያገኘሁት በ Tower in the sky መጽሀፍ ላይ ካደረጉት የመጨረሻ ክፍል ውይይት ነው፡፡

ጉዳዩም የህይወት ተፈራ Tower in the sky ዘመኑን ከሚያሳዩትና ኪነ ጥበባዊ እሴቱንና ሥነ ጹሁፋዊ ለዛውን ከተመለከተው ጉዳይ በተለይ ፍልስፍናዊ አተያዩ ምን ይመስላል? በሚል ከጋዜጠኛ ህይወት ፍሬስባሃት ጥያቄ የቀረበላቸው ዶ/ር ዳኛቸው ገለጻቸውን የጀመሩት በአንድ ታዋቂና አለም አቀፍ የማህበረ ሳይንስ ፈላስፋ/ sociologist/ ትርክታ ነው፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው እንደተናገሩት ከሆነ ይህ ፈላስፋ ፖለቲካ ሁለት አተያዮች እንዳሉት ይገልጻሉ፡፡ ሃላፊነት የተሞላው ፖለቲካ /political responsibility/ እና ፍጹማዊ ፖለቲካ /political absolute/በማለት ፡፡

የመጀመሪያው ሃላፊነት የተሞላው ፖለቲካ /political responsibility/ የሚባለው እይታ መድረሻና መነሻውን የሚያውቅ፤ ወደግቡ የሚያደርሰውን መንገድ ሁሉ ሃላፊነት በተሞላበት አኳኋን የሚራመድና ሥህተቱንም እያረመ የሚጓዝ አይነት ሲሆን፣ ፍጹማዊ ፖለቲካ /absolute politics/ የሚባለው ደግሞ መነሻና ሂደቱ ምንም ይሁን ምን ግቡ ላይ ለመድረስ መፈንቀል ያለበትን ሁሉ

ያለምንም ሃላፊነትና ሞራላዊ ስሜት እየፈነቀለ የሚሄድ፤ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ዓይነት አካሄድ የሚከተል፤ እሱ የሚለው ብቻ ትክክል ሌላው ሁሉ ውሸትና አይረቤ ነው ብሎ የሚያምን መሆኑን ፈላስፋውን በመጥቀስ ያብራሩት ዶ/ር ዳኛቸው ይህ አተያይ በተለይ ለሃገሬ ጋዜጠኞች ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ነው ብዬ አስባለሁ በማለት አጋጣሚውንም እንደማሳያ እንዲህ ሲሉ (ቃል በቃል ባይሆንም) አቅርበዋል፡፡ አንዳንድ ጋዜጠኞች ይጠይቁንና ሃላፊነት በጎደለው መንገድና ሞራላዊ እሴቱ በወረደ ደረጃ ከሳይንስም ከግለሰብም ንግግር የወጣ ነገር ይጽፋሉ፡፡ እንዴት? ብለን ስንጠይቃቸውም "ተው ባክህ ሞቅ ይበል ብለን ነው" ይሉኛል በማለት፡፡

አሁንም በሃገሬ ያለው ጋዜጠኝነትና ፖለቲከኛነት የዚሁ ተመሳሳይና ፍጹማዊ ፖለቲካ /absolute politics/ የሚለውን እይታ የሚከተል ይመስላል፡፡ በተለይ ከሰሞኑ ደግሞ በሠላማዊ ሰልፍና በሙስሊሞች መብት ስም የሠላማዊ ሰልፍ ሥር ቁማርተኞች በዝተዋል፡፡ አንዳንድ ፕሬሶች እና አምደኞቻቸውም ሞቅ ባለበት ሞቅ እያሉ ሃላፊነት በጎደለው መንገድ ይጽፋሉ፡፡ የጋዜጣው ወይም መጽሔት ባለቤቶች ዶ/ር ዳኛቸው እንዳሉት ጉዳያቸው ከትርፋቸው እንጂ ከነባራዊው ማህበረ እሴት ስላልሆነ ሞቅ ተደርጎ የተሰጣቸውን እንቶ ፈንቶ ይበልጥ አጋግለው ያትሙታል፣ለንግድና ለትርፍ ገበያ ያወጡታል፡፡ ትክክለኛ ነው ስህተት ወይስ ሌላ አይገባቸውም፤ ህግ መንግስታዊ አንቀጾች በማይገቡባቸው ቦታዎች እየጠቃቀሱ አንዱ ያሰማውን መፈክር የሽፋን ገፃቸው ማድመቂያ በማድረግ፤ ያልነበረውን እንደነበር፤ያልተነገረውን እንደተነገረ፤ አድርገው ይጽፋሉ፡፡

በተለይም ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ጉዳዮችን ህብረተሰብ እንደህብረተሰብ እርሥ በርሥ ሊያጋጩ የሚችሉ ጉዳዮችን ሳይመዝኑና ሳያረጋግጡ በመጻፍ ፕሬሶቹ ለትርፋቸው፤ ጋዜጠኞቹም ለሆዳቸውና ጊዜያዊ ስሜታቸው፤ ተቃዋሚዎቹ ለአቋራጭ ስልጣናቸው፤ አክራሪዎቹም ለተከፈላቸው ሂሳብ ማወራረጃቸው ሲሉ በሰላማዊ ሰልፍ ስምና በ"ሰማያዊ ጃንጥላ" ተጠልለው ቁማሩን ተያይዘውታል፡፡ የጆከርነት ድርሻቸውንም በየሰዓቱና በየቀኑ በመለዋወጥ እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡  ከሚመጣው ሁሉ ለመጠቀምም ሁኔታዎችን ማጋጋል ነው፡፡ ልክ እንደ ጆርጂያ፤ ልክ እንደ ታህሪር  የቀለሙን ዓይነት ባይናገሩትም በፋክት፤ በአዲስ ጉዳይ፤ በኢትዮ  ምህዳር፣ ፍኖተ ነፃነት፤ ድምፃችን ይሰማና ኢሣት   አያይዘው የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረስ ነው አላማቸው። ለዚህ የተገኘውና ብቸኛው አማራጭ ደግሞ በእነርሱ ዘንድ የሠላማዊ ሠልፍ ሥር ቁማርና ቁማርተኝነት ነው፡፡ ፍጹማዊ ፖለቲካ /absolute politics/ን ለመተንተን በኢ.ድ  ማግስት ከወጡ ፕሬሶች ሁለቱን ብቻ እንደማሳያ እንጠቀማለን፡፡ ፋክትንና አዲስ ጉዳይ የተሠኙ መጽሔቶችን።

አቋማሪው የቀለም አብዮት ነው፡፡ ቁማርተኞቹ ደግሞ የከሰሩ ፖለቲከኞች፣ አክራሪዎች፣ አንዳንድ የግል ፕሬሶች እና አምደኞቻቸው ናቸው፡፡ አጫዋቹ ጆከር ደግሞ ሁለት ነው፡፡ የፖለቲካ ፖርቲዎች በሆኑት ሰማያዊና አድነት። በሠሞነኛቅው ሠላማዊ ሰልፍ ሥር የተደረገው የቁማር ጨዋታ አክራሪነትን የሚያጎላና ያስተናገደ የነበረ መሆኑ በአደባባይ የታየ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ከቁማርተኞቹ አንዱ የሆነው አምደኛ በቁማርተኛው ፋክት መጽሔት ላይ ይህን ሃቅ በመተው "የፓሪቲዎች ኃላፊነት የግለሰቦችን አልያም የቡድኖቹን ብሦት አስተባብሮ ወደ አደባባይ ይዞ መውጣት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአደባባይ የታየውም ይሄው ነው" በማለት ካርታውን ይሰርቃል፡፡ የዚሁ ቁማርተኛ አጫዋች የሆኑት ሠማያዊ ፓርቲና አንድነትም የጫዋታውን ውጤት በተመለከተ "ኢህአዴግ በሚከተለው የፖለቲካ ስርዓት ምክንያት የህዝቡ ስነ ልቦና በከፍተኛ ደረጃ የተሸነፈ ነበር፡፡ ህዝቡ መንግስት እያደረገበት ስላለው ጫና ከማሰብ ውጪ እርሱ ማድረግ ስለሚችለው ነገር ማሰብ አቆቶታል፡፡ ፓርቲው ባካሔደው ሠላማዊ ሰልፍ በዋናነት የለወጠው ነገር ይህን አስተሳሰብ መቀየር መቻሉ ነው። በሠልፉ ምክንያት ህዝቡ ከፍርሃት ቆፈኑ እየተላቀቀና ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን እየጠየቀ ነው፡፡ ህዝቡ ለመንግስት አጭር መልዕክት አስተላልፏል፡፡ የሠጠውህን ኮንትራት ለማፍረስ መብቱ አለኝ የሚል ነው፡፡ ለስምንት ዓመት የታፈነ የህዝብ ድምፅ መጮህ ችሏልና ይሄ ዋነኛው ስኬታችን ነው" ብለዋል፡፡

እዚህ ላይ "ህዝብ" የተባለውና "ስምንት ዓመት የታፈነ ጩኸት" የሚሉት ነጥቦች መፍታታት አለባቸው፡፡ በሰልፉ ላይ ያየናቸው ጥቂት አክራሪዎችን እንጂ 80 ሚሊዮን የሆነውን ህዝብ የሚወክሉትን አልነበረም፡፡ በርግጥ ህገወጥ ወደሆነው ቁማር የተወሠኑትን ቀላቅለዋል፡፡ ስኬት ከተባለም ያለው ሃቅ ይኸው ነው፡፡ የአንድነቱ አቶ አሥራት እንዳሉትም ግባቸው ማስጮህ ነበርና ማሰባሰብ የቻሉትን ያህል አስጬኸው ህዝቡን አስጬኸናልና ስኬት ነው ካሉም ትርፉ ትዝብት ነው ብለን እንለፋቸው፡፡ ዳሩ ግን እራሣቸው አቶ አስራት የሚመሩት የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ያደረጉትን ሠላማዊ ሠልፍ ዘንግተው የታላቁን መሪ ስራ ለማጠልሸት ስምንት ዓመት የታፈነ ድምጽ ወይም የተከለከለ ሠልፍ ማለታቸው በርግጥም የቁማርተኝነታቸው ደረጃ የት ጫፍ እንደደረሠ የሚያሳይ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በዚሁ ቁማር ላይ ያለው የሠማያዊ ፓርቲና የአንድት ፓርቲ የበላይነትን ለመውሠድና እኔ ነኝ ለማለት የሚደረገውን የትምክህት ቁማር ያነበብነው ከዚሁ ቁማርተኛ ከሆነው ፋክት መጽሔት ነው፡፡ ቁማርተኛው አምደኛ እንዲህ ሲል ለቁማርተኞቹ ጥያቄ ያነሣል "እነዚህ ፓርቲዎች (ቁማርተኞች) በተበጣጠሠ እና በተለያየ መልኩ የተቃውሞ ሠልፎችን ከማድረግ ይልቅ ለምን ህብረት አይፈጥሩም?" ቁማርተኞቹም ይመልሣሉ የአንድነቱ "አዎ የታንጎ ዳንስ ያስፈልጋል" ሲሉ ሠማያዊ ቁማርጠኛው ደግሞ "ሰልፍ ግብ ሳይሆን መንገድ ነው፡፡ አንድነት ፀረ ሽብር አዋጁን ለማሠረዝ ይንቀሣቀሣል፡፡ እነርሡ አንዱአለም የታሠረበትን

ቀን እያሰቡ ሠላማዊ ሠልፍ ሊያደርጉ ሢያስቡ እኛ ሠዎቹ እንዲፈቱ በማለት ሠልፍ እናደርጋለን፡፡ እነርሡና እኛ ሰልፍ የምናደርግበት መንገድም ዓላማም ይለያያል፡፡ የመንፈስ አንድነት እና የዓላማ ተጋሪነት ከሌለህ እንዴት ብለህ በአንድ ላይ ትቆማለህ፡፡ የአመራሩ በቃት የሥነ ልቦናና የአደረጃጀት ደረጃ እኛ ከእነርሱ በብዙ ነገሮች ፈጽሞ የተለየን ነን፡፡"

ይህ ነው እንግዲህ ቁማርና ቁማርተኝነት፤ ሁለቱም በሠላማዊ ሠልፍ ሥር የተንጠላጠሉ ቁማርተኞች ናቸው፡፡ ሁለቱም ህዝብ ህዝብ ይላሉ፡፡ ሁለቱም የእምነት ነፃነት እያሉ ለቁማር መድረካቸው ስልት ያሠናዳሉ፡፡ ግን ደግሞ አንዱ እኔ ፍፁም የተለየሁና ሠማያዊ ነኝ ይላል፡፡ ህዝብ ህዝብ እንዳላሉ እና ቀደም ብለው እንዳልተሞከሻሹ አሁን ደግሞ የመንፈስ አንድነትና የዓላማ ተጋሪነት የሌላቸው መሆኑን ያወጋሉ፡፡ ታዲያ ህዝብ መቆመሪያ መሆኑን ዓላማና መንፈሣቸው ግን አብዮት መሆኑን ከዚህ በላይ ማን ይንገረን፡፡ የአንድነት ምድራዊ ቁማርተኛ የአብሮነትን አስፈላጊነት በታንጎ ዳንስ ቢመስልም ግባቸው ግን ዶ/ር ዳኛቸው እንዳሉት Absolute politics ነው፡፡

ምክንያቱ ቢሉኝ ደግሞ በርግጥም ቁማርተኛው እንዳሉት ስልጣን ኮንትራት ነው፡፡ ህዝብ የሠጠውን የኮንትራት ስልጣን የመንሣት መብት ያለው መሆኑም ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ግን ደግሞ ስልጣን መንሣት የሚችለው ኮንትራቱን በሠጠበት መንገድ ነው፡፡ ኮንትራቱን በምርጫ የወሠደው ፓርቲ ኮንትራቱን ማራዘምም ሆነ ማስረከብ የሚችለው የተሠጠው ጊዜ ሲያበቃ በሚደረግ የኮንትራት ማራዘሚያና መንሻ ምርጫ ሆኖ ሣለ አቶ አስራት ኮንትራቱን በፈለገው ሠዓት ማንሣት ይቻላል፤ በማለት ህገወጥ የሆነውን ቁማር መጫወታቸውን ከዚሁ ቁማርተኛ ከሆነው ፋክት መጽሄት ላይ ጠቅሼ ቀደም ሲል አመልክቻለሁ፡፡

Political Responsibilities መነሻና መድረሻው መንገዱም ግልጽ ነው፡፡ ልክ እንደሰለጠኑት ሃላፊነት የተሞሉ ፖለቲከኞች በምርጫ ቦርድ መመዝገብ፤ ፕሮግራምና ፖሊሢዎች ቀርጾ ለህዝብ ማስተዋወቅ፤ ህዝቡን መቀስቀስና መወዳደር፣ አማራጩን የለየ ህዝብ ደግሞ የሚበጀውን መምረጥና ኮንትራት ማራዘም አልያም ከሌላው ጋር መፈራረም ትክክለኛው መንገድ ነው፡፡

በአወልያና መጅሊስ በተነሣ የአክራሪነት እንቅስቃሴና ህግና ሥርአት በማስከበር መካከል ያለ ሁኔታን በማራገብ በሠልፍ ጥላ ሥር አክራሪያኑን መጋበዝና የተቀደደ ባንዲራ አስይዞ ማስጮህ፤ የሃገር መለያና የሉዓላዊነት መገለጫ የሆነ ባንዲራ ሲቃጥል "ማን ያራከሠውን" ብሎ መሟገት በርግጥም የስውር አጀንዳቸው ነጸብራቅ ከመሆኑ በስረቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም። ታላቁ መሪ በአንድ ወቅት ብለውት የነበረው እኮ "ባንዲራ የተሠራው ከጨርቅ ነው፣ ግን ደግሞ ከጨርቁ በስተጀርባ ያለው ክብር እሴትና መገለጫ ነው መታየት ያለበት" ነበር ያሉት፡፡ ይህ

ደግሞ ትክክል ነው። ሃገር ሲባል እኮ ተራራው መሬቱ ጋራ ሸንተረሩ ለብቻው ማለት ደይደለም፡፡ ወይም ውክልናው ግዛት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ በላይ ያለው ህዝብ፤ ህብረተሰብ፤ ልዕልና፤ ባህል፤ ዕሴት፤ ቋንቋ፤ እምነት ወዘተረፈ ነው፡፡

ቁማር ቁማር ነውና ጨዋታውም መስረቅና ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው absoliute politics በመሆኑ ለበጎ የተገለፀውን የባንዲራ ማብራሪያ ለክፉ በመጠቀም፤ ሆኖም እንኳ ቢሆን አንዱ ስላራከሠ ሌላውም ያቃጥለው ብሎ ለመሞገትና ጥቅም ላይ ለማዋል መሞከር ከነዚህ ሃይሎች የሚጠበቅ በመሆኑ አይገርመንም፡፡ እዚህ ጋር ቁማርተኛው አምደኛ ቁማርተኛ የሆኑት አጋር ፓርቲዎቹ በርግጥም ቁማር እየተጫወቱ ስለመሆኑና ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው "ህዝቡን አነቃንቋል ግቡም ይኸው ነበር፣" ሲሉ ያብራሩትን በመዘንጋት እሳቸውም ቁማርተኛ እነርሡም በሠላማዊ ሠልፍ ሥር የተሠባሠቡ ቁማርተኞች ስለመሆናቸው እንዲህ ሲሉ በቁማሩ ማጠናቀቂያ ላይ ገልጸዋል፡፡ "የየፓርቲዎቹ አመራሮች በከፊል ፍርሃት ውስጥ ሆነው ህገመንግስታዊ መርሆዎች ብቻ እንዲከበሩ የሚጠይቁ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዋነኞቹ የሠልፎቹ ተሣታፊዎች መሆናቸው እና ፓርቲዎቹ ሌሎቹን የማህበረሰብ ክፍሎች አነቃቅተው ለማስተባበር አልቻሉም፡፡" በሌላም በኩል በማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሄት ስለመሆኗ በፊት ገጿ የምትናገረው አዲስ ጉዳይ ዶ/ር ዳኛቸው እንዳሉት ሞቅ ለማድረግ ወይም Absolute Politicsን ጨዋታ ለመጫወት የሽፋን ገጿን በመስጊዶችና በሦላት ሠጋጆች አደማምቃ ከሙስሊሞች ጉዳይና ሠለፊያ ጋዜጣ በባሠ ደማምቃ መውጣቷ ከመነሻው ቁማርተኝነቷን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህችው በፖለቲካ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩራለሁ የምትለው አዲስ ጉዳይ በ97 ምርጫ ማግስት እንደምናስታውሣት መዝናኛ ጋዜጣ ወደፖለቲካ ያደረገችውን የሞቅታ ለውጥ አዲስ ጉዳይም በኢድ ማግስት ከ50 በመቶ በላይ የሆነውን ሽፋን ርዕሠ አንቀጿን ጨምሮ የሠጠችው በሠላማዊ ሠልፍ ሥር ለተጠለሉቱ ቁማርተኞች ሲሆን፤ ድምፃችን ይሰማና ሌሎች የአክራሪያኑን መገናኛ ዘዴዎችም እግረመንገዷን በማስተዋወቅ የአወሊያውና የአክራሪያኑ ምሽግ መሆኗን አስመስክራለች፡፡